# ሹም ጓንጉል

ወያኔ ያሳደገው ፣ ጡቱን እያጠባ
ተንፍሶ ያደገ ፣ በነመለስ ሳንባ
እንደእስስት ቢለወጥ ፣ ቢቀይርም ካባ
የቀለም አይነቶች ፣ ሺጊዜ ቢቀባ
መቼም ፎቀቅ አይልም ፣ ከተንኮል ከደባ
ከፍ ሲል ገዳይ ነው ፣ ዝቅ ካለም ሌባ
እንኳን ላገር ሊበጅ ፣ ለራሱም አይረባ ።

ሰኔ ሰኞ ገጥሞ ፣ ዛር ቆሞለት ስናይ
አቋም የሌለውን ፣ የመጣን አታካይ
አንቱ የተባለን ፣ ወስላታ ወላዋይ
በመዝረፍ አንደኛ ፣ ጨካኝ ቢሆን ገዳይ
ለጆሮ የሚጥም ፣ ቃል ካሰማ ላዋይ
ያላትን ቃል ይዘን ፣ የትላንቱን ሳናይ
ከማጨብጨብ በቀር ፣ ማንም ሰው አይልም ሃይ
መሃል የሚገባም ፣ አይታይ ገላጋይ ።

ሀሰት እያቀላ ፣ እውነት እያደላ
ጨዋታው አይጥምም ፣ እናዝናለን ኋላ
ይቅርታን በመስበክ ፣ ባንድነት ከለላ
ከወያኔም ሳይርቅ ፣ ከህዝብ ሳይጣላ
እዚህም እዚያምጋ ፣ ተክሎ ሁለት ባላ
አንደኛው ቢከዳው ፣ በሌላው ሊበላ
በቃል ተሸውደን ፣ ዛሬ ካልነው ችላ
በጊዜ ካልነቃን ፣ በግ ነው ያልነው ተኩላ
እንኳንስ በሰላም ፣ አይወርድም በዱላ ።

የስካሁኑ አካሄድ ፣ ምስክር ካልሆነ
ዛሬም ካልተማረ ፣ ወያኔን ካመነ
አምርሮ ሊታገል ፣ ህዝቡ ካልጨከነ
የመቀሌው ደባ ፣ በንጭጭ ካልመከነ
ትግሉ እየቀጨጨ ፣ እየመነመነ
መተንፈሻ ጠፍቶ ፣ ህዝብ እንደታፈነ
ያሰጋል እንዳይኖር ፣ ዳግም እንዳዘነ ።

ከአባብ እንቁላል ፣ እርግብ መች ይገኛል
መከራው የጠና ፣ አይሆኑ ይመኛል
የወያኔ ሴራ ፣ ዕፁብ ድንቅ ያሰኛል
ተንኮል ተከኖበት ፣ ብልጡንም ያሞኛል
ጎትተው ያመጡት ፣ አልጥምህ ብሎኛል
ሹም ጓንጉልን ማጀብ ፣ አይበጅም ቀፎኛል ።

ታዛቢው

May 27, 2018